AMHARIC

Infosheet 6. Rejection

# መብቶትን ይወቁ

## አሉታዊ ውሳኔን ከተቀበሉ በኋላ

LEGAL CENTRE LESVOS

ይህ የመረጃ ሉህ በሌስቮስ፣ ግሪክ በሚገኘው የድንበር ሂደት ውስጥ በተተገበረው የጥገኝነት ሂደት ላይ አሉታዊ ውሳኔ ከተቀበሉ በኋላ ስለመብቶችዎ አጠቃላይ መረጃ ይዟል።

በግሪክ ህግ ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረተ እና ከጁላይ 1 2021 ጀምሮ ትክክለኛ ነው።

የመረጃ ሉህ የተሟላ አይደለም እና ለለውጦችም የተጋለጠ ነው። በግሪክ ውስጥ ሕግ ለማተግበር ፈቃድ ያለው ጠበቃ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ስለጉዳይዎ ነፃ የሕግ ድጋፍ የሚሰጥ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እንዲያማክሩ እንመክርዎታለን።

- የጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ አሉታዊ ውሳኔ (ውድቅ) ከተቀበሉ፣ **ጉዳይዎ እንደገና እንዲታይ ለመጠየቅ ይህንን ውሳኔ መቃወም ወይም ይግባኝ ማለት ይችላሉ።**
- ይህን ለማድረግ፣ እንደ **የጥገኝነት አሰራርዎ ደረጃ ላይ በመመስረት** የተለያዩ መፍትሄዎች ለእርስዎ ይገኛሉ።
- ይህን ለማድረግ የሚገደዱበት **ቀነ- ገደቦች** አብዛኛውን ጊዜ የሚጻፉት በውሳኔዎ **መጨረሻ ላይ በእንግሊዝኛ ነው።**

የመጀመሪያ ደረጃ ውድቅ

ከተደረጉ (ከቃለ ምልልስ በኋላ)

- ይህን ውሳኔ ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ **"ይግባኝ" በማስገባት** ለመቃወም **10 ቀናት** አለዎት።

- ይህን ለማድረግ፣ ይግባኝ ማለት እንደሚፈልጉ የሚገልጽ **የጥገኝነት ቢሮ ያቀረበውን ሰነድ መፈረም አለብዎት።**

- በዚህ ይግባኝ ላይ እርስዎን የሚወክል **የክልል ጠበቃ ከክፍያ ነፃ የማግኘት መብት አልዎት**። ውሳኔዎን ይግባኝ ለማለት ሰነዱን ሲፈርሙ ጠበቃ ለማግኘት ይጠይቁ።

- ይግባኝዎ **በአቴንስ ካሉት የይግባኝ ባለስልጣን ኮሚቴዎች** ውስጥ በአንዱ ይመረመራል።

- **የችሎት ቀን** ከእርስዎ ጋር ይጋራል እና ይግባኝ ለማለት በፈረሙበት ወረቀት ላይ ይጻፋል።

- የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው ጉዳይዎን በድጋሚ የሚመረምረው በእርስዎ ጉዳይ ላይ በተጻፉት የጽሁፍ ሰነዶች ላይ ነው። በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች፣ ለይግባኝዎ የቃል ችሎት አይኖርም፣ ነገር ግን በአንዳንድ በጣም አልፎ አልፎ፣ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው የቃል ችሎት ለመከታተል በይግባኝ ምርመራው ወቅት እንዲገኙ ሊጠይቅ ይችላል። ጉዳዩ ይህ ከሆነ፣ ይህንን እድል እንዳያመልጥዎት እና ከተቻለ አብሮዎ እንዲሄድ ጠበቃ ያማክሩ።

- **የነጻ የክልል ጠበቃ ተመድቦልዎ ከሆነ፦**
    - የጠበቃው  አድራሻ ዝርዝሮች ይጠይቁ።
    - ከጠበቃው/ ሷ  ጋር ቀጠሮ ለመያዝ ሞክሩ፣ ጉዳይዎን ለማስረዳት፣ ማንኛውንም ተጨማሪ ወይም አዲስ መረጃ እና የጥገኝነት ጥያቄዎን የሚደግፉ ሰነዶችን ያቅርቡ፣ በጥገኝነት ቃለ-መጠይቅዎ ወቅት የተሳሳቱትን ማናቸውንም ማብራራት እና አስፈላጊ ማብራርያዎችን ይስጡ።
    - የመንግስት ጠበቃ ማንኛውንም ስህተት ለመቃወም  እና ይግባኝዎን በህጋዊ መንገድ ለመደገፍ የጽሁፍ ማስታወሻ ያዘጋጃል። እሱ/ ሷ የይግባኝዎ ምርመራ ከተካሄደበት ቀን በፊት ይህንን ማስታወሻ ያስገባሉ።
- **የነጻ የክልል  ጠበቃ ካልተመደበልዎ**፣ ነፃ የህግ ድጋፍ በሚሰጥ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም በግሪክ ጠበቃ በኩል የሕግ ምክር ለማግኘት ሞክሩ።

ሁለተኛ ደረጃ ውድቅ ከተቀበሉ

(በይግባኝ ኮሚቴ የተሰጠ)

የሁለተኛ ደረጃ ውሳኔን በሁለት አማራጭ መንገዶች መቃወም ትችላለህ፡-

**1/ ለመሻር ማመልከቻ (ወይም አስተዳደራዊ ይግባኝ)**

- ❖ **የመሻር ማመልከቻው አሉታዊ ውሳኔው በተገለጸ በ30 ቀናት ውስጥ** ለግሪክ አስተዳደር ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት።
- ❖ እባክዎን ሁሉም ሰው **እንደዚህ አይነት ይግባኝ ማቅረብ እንደማይችል ልብ ይበሉ፡ ውድ ነው (በአብዛኛው የህግ እና የፍርድ ቤት ክፍያዎችን መሸፈን አለብዎት) እና ይግባኙ ጥብቅ መስፈርቶች አሉት፡** በጉዳይዎ አያያዝ ላይ የሥርዓት ወይም የህግ ስህተቶች ሊኖሩት ይገባል።
- ❖ በዚህ ሂደት ውስጥ እርስዎን የሚወክል <u>የግሪክ ጠበቃ ሁል ጊዜ ያስፈልግዎታል።</u>

## 2/ ቀጣይ ማመልከቻ

የእርስዎን ጉዳይ የሚደግፍ **አዲስ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ አለቦት።** ይህ ማለት:

- ❖ በመጀመሪያው ቃለ መጠይቅዎ ወቅት ያላስገቡት እንደ **አዲስ የህክምና ሰነዶች፣ አዲስ ማስረጃዎች ወይም ስለእርስዎ፣ ስለቤተሰብዎ ወይም ስለትውልድ ሀገርዎ ወዘተ ያሉ አዳዲስ መረጃዎች።**

- ❖ ይህ አዲስ ማስረጃ የጥገኝነት ጥያቄዎን **ለመደገፍ አስፈላጊ እና የጉዳይዎን ውጤት ለመለወጥ በቂ መሆን አለበት።**

- ❖ ይህን አዲስ ማስረጃ **ለምን እንዳላካፍላችሁ ወይም እንዳልተቻላችሁ** (በመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ እና ይግባኝ ወቅት) ማስረዳትዎ አስፈላጊ ነው።

- ❖ የግሪክ ጥገኝነት ቢሮ በመጀመሪያ ያቀረቡት ማመልከቻ **“ተቀባይነት ያለው”** መሆኑን ይመረምራል፣ ይህ ማለት እርስዎ ጉዳይዎን እንደገና ለመገምገም በቂ የሆነ አዲስ ማስረጃ ማቅረብ ችለዋል ወይ ማለት ነው።
- ➢ ቀጣዩ ማመልከቻዎ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ፣ **ማመልከቻዎን እና የቀረበውን ማስረጃ ለመገምገም አዲስ ቃለ መጠይቅ ይኖርዎታል።**
- ➢ **የግሪክ ጥገኝነት አገልግሎት ጥያቄዎ ተቀባይነት እንደሌለው ካገኘው** ወይም ተከታዩ ማመልከቻዎን ካልተቀበለው በዚህ ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ (ለዚህ ከላይ ያለውን "የመጀመሪያ ደረጃ ውድቅ ካደረጉ) ይመልከቱ።

LEGAL CENTRE LESVOS

**ዋትስአፕ:** +30 694 961 8883
**መስመር ስልክ:** +30 225 1040 665
**Email:** info@legalcentrelesvos.org
**Facebook:** www.facebook.com/LesvosLegal
**አድራሻ:** Sapfous 2, Mytilene 81100
**Opening Hours:** Monday to Friday - 10am to 2pm